ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

Solidarity Movement for a New Ethiopia

---

## የታቀደው የኢትዮጵያ ጉዳየኞች የትብብር ስብሰባ ጥሪ ተሰርዟል!

ከጥቂት ሣምንታት በፊት ለአዲሲቷ የጋራ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ፣ ይመለከተኛል የሚሉ ጉዳየኞች በአንድ ቦታ ተሰባስበው የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ የሚመካሩበትን መድረክ ለማመቻቸትና መነገዱን ለመጥረግ የሚያግዝ ጉባኤ ለማድረግ ለ**መገናኛ ብዙሐን (የፓልቶክ ክፍሎችንም ጨምሮ) ፣ ለፖለቲካ ድርጅቶች ፣ ለእርነት ንቅናቄዎች ፣ ለሲቪክ ድርጅቶች ፣ ለሴቶችንና ወጣቶች ማኅበራት ፣ ለሃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም ለአገር ሽማግሌዎችን እና ሌሎች ለአገራችን ቅን የሚያስቡና ለነጻነቷ የሚታገሉ** ሁሉ ጥሪ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ ንቅናቄው ይህንን ጥሪ ባስተላለፈበት ወቅት የማስተባበር ኃላፊነቱ የወሰደ በመሆኑ ጥሪው ለሁሉም ወገኖች እንዲደርስ በመደረጉ በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች – በድረገጾች ፣ በፓልቶክ የመወያያ ክፍሎች ፣ ወዘተ በጉዳዩ ላይ የጠለቀ ወይይት አንዳንዴም ክርክር ሲካሄድበት ሰንብቷል፡፡

ሆኖም ግን ጥሪው ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ እስካሁን የየትኛወም የፖለቲካ ድርጅት ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን ጥቂት የሲቪክ ድርጅቶች ግን ያላቸዉን ድጋፍና ፈቃደኝነት ገልጸወልናል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ከህዝቡ ያገኘነው አበረታችና በጎ ምላሽ ከፖለቲካ ድርጅቶች ይልቅ ህዝባችን ለትብብር ምን ያህል ፍላጎት እንዳለው ያሳየበት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቅስ የማናልፈው ሐቅ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ከምንግዜወም በበለጠ ሁኔታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፣ አፈና፣ ግድያ፣ እስራት፣ ወዘተ እየተባባሰ የመጣበት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ባለፈው ተካሄደ በተባለው <<ምርጫ> ህወሃት/ኢህአዴግ 99.6 አሸነፍኩ ብሎ ሁሉንም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፖለቲካ እንቅስቃሴ አስወግዶና የፖለቲካ ምህዳሩን ዘግቶ ባለበት ወቅት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚሉ ሁሉ ሊተባበሩ አብረው ሊሠሩ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ከሃዘንና ምሬታችን ወስጥ ያገኘነው ጣፋጭ አጋጣሚ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ኃይላችንን ከማስተባበር ይልቅ – በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች – ለዘመናት ጠፍሮ በያዛቸው የዓምባገነንነት አባዜ ተወጥረዉ የጎሪጥ እየተያዩ እርስበርሳቸው በመጠላለፍና በመካሰስ ለመቀጠል ሜፈለጋቸው <<በእርግጥ እየታገሉ ያሉት ማንን ነው>> ብለን እንድንጠይቅ አድርጎናል፡፡ ለቀረበው ጥሪ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ሜልስ ለማስጠት አለሜፈለጉ ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ራሣችን ችግር እንዳለብን በራሱ የሚጠቁም ሲሆን፤ ይህም ችግር የመጣብን ከሌሎች ጋር መተባበር የእኛን ኃይል የሚያዳክምና የሌላወን የሚያጎለብት ማስሎ ስለሚታየን፤ እንዲሁም ሌሎች በትግሉ ወስጥ ያሉትን ወገኖች የጋራ ሀገራዊ ጥቅም ተካፋይ አድርጎ ከመሜልከት ይልቅ ተቀናቃኝ ባላንጣ አድርገን በሜፈረጃችን ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጠባብ አመለካከት በተኮፈሱ ድርጅቶችና መሪዎች ቅኝት ትግላችን የትም መድረስ እንደሜይችል የተገነዘቡ የፖለቲካ መሪዎች ስለመኖራቸዉ ጥያቄዉን ለራሳቸው እንድንተወው አስገድዶናል፡፡ በበኩላችን ተቀራርቦ ላለመጋገርና ላለመተባበር ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱትም ሆነ ከሌሎች ሰንካላ አስተሳሰቦች አኳያ የእያንዳንዱ ፖለቲካም ሆነ የሌላ ድርጅት አባል እንዲሁም ሕዝቡ ባጠቃላይ ለመተባበር እንቅፋት የሆኑበትን ድርጅቶችና መሪዎች በግልጽ ሊተቻቸው ፣ ሊያጋልጣቸውና በኃላፊነት ሊጠይቃቸው ይገባል እንላለን፡፡ <<ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነት>> የቀደመባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንመሠርታለን ብለን የምናስብ ከሆነ በአዲስ አስተሳሰብ መሳትና ችግሮቻችንን በግልጽ አንስተን መወያየትና መተቻቸት አለብን፡፡ ይህም ከራሣችን ጀምሮ እስከ መሪዎቻችን ድረስ ሊዘልቅ ይገባል፡፡

ምንም እንኳን ንቅናቄያችን ጥሪ ካቀረበላቸው ጉዳየኞች በተለይም ከፖለቲካ ድርጅቶችና የግምባር ንቅናቄዎች አጥጋቢ ምላሽ ባለማግኘቱ በቅርቡ ለሚድረግ ያሰብነ ወኝ ታላቅ የትብብር ስብሰባ የሰረዘ መሆኑን ቢያስታወቅም በቀጣይነት ይህንን የትብብር መድረክ ለመፍጠር የሚያደርገ ወኝ ጥረት እንደሚ ፋበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ በተለይም ለዓመታት ከፖለቲካወና አገራዊ ጉዳዮች ተገልለው የኖሩ የወጣቶችን እንዲሁም የሴቶችና የሃይኖማት ድርጅቶችን የማስተባበር ሂደት ንቅናቄአችን በትጋት ለመቀጠል ቆርጦ መነሳቱን ለመግለጽ ይወዳል፡፡ ከዚህ አኳያ በቅርቡ እየተቋቋሙ ያሉ የወጣት ፣ ሴቶችና ሌሎች ድርጅቶች የምናበረታታ ሲሆን፤ በቅርቡ የኦሮሞና የአፋር ድርጅቶች ትብብርን አስመልክቶ ያወጡትን መግለጫ የምንደግፍ መሆናችንና ሌሎችም ድርጅቶችና ንቅናቄዎችም ይህንን ፈለግ እንዲከተሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

በመጨረሻም ንቅናቄያችን የጀመረወኝ የትብብር መድረክ ለመፍጠር በሚያደርገዉ ጥረት ተመሳሳይ ተግባር የጀመሩና ወደፊት ለመጀመር ከሚያስቡ ጋር ተባብረን ለመሥራት ያለንን ፍላጎት በድጋሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ ለዚህም ወገንን የማዳን ጥሪ አፋጣን ምላሽ በማስጠት ሕዝባችን ለዘመናት ሲናፍቀው የኖረወኝ ነጻነት ዕወኝ በሚድረግ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም ሊያስገኝ በሚችል ተግባር ሁላችንም ቀና ወሳኔ ለሚድረግ እንድንችል ፈጣሪያችን ይርዳን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር



አባንግ ሜቶ
ዋና ዳይሬክተር
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
*****************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ* ***የንቅናቄወኝ የዕርቅ ግብረኃይል*** *በ (reconciliation@solidaritymovement.org) ወይም ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ አባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለሚዳት ይችላሉ፡፡*

